# የዓረና ትግራይና የት.ዴ.ት/ታንድ/ ወቅታዊ መግለጫ፤

## ግፍ እስከ መቼ?

የህወሐት አመራር ለ27ዓመታት ኢህአዴግን በበላይነት እየመራ በመላው ኢትዮጵያ የግፍ አገዛዝ አንግሶ፤ ህዝቡን ለከረፋ ኑሮ፣ ለእርስ በርስ ግጭት፣ ለአሳፋሪ ስደት እንደዳረገው እንዳለ ሆኖ የኢትዮጵያ ህዝቦች ባካሄዱት ያልተቋረጠ ትግል ከውስጥ ተገፍቶ የአመራሩን ስልጣን እንዳጣና ለስልጣን ላበቃው በትግራይ ህዝብ ብብት ውስጥ ተወሽቆ ወደ ነበረበት ለመመለስ የሞት ሽረት ትግል እያካሄደ እንደሚገኝ የየእለት ተግባሩ ይመሰክራል፡፡

በመላው ኢትዮጵያ እየነፈሰ ያለው የለውጥ አየር ወደ ትግራይ ዘልቆ እንዳይገባና ህዝቡ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ ሙብቱ አስከብሮ የመፃኢ እድሉ ወሳኝ ባለቤት እንዳይሆን የህወሃት አመራር በግፍ ላይ ግፍ እየፈፀመ ሽብርተኛ አገዛዙን በስፋት ቀጥሎበታል፡፡ ሰሞኑን ያወጣዉን መግለጫ ልብ ብሎ ለተመለከተ ሰው ይህንኑ ሽብርተኛ መልእክት እያስተጋባ መሆኑን በግልፅ ይታያል፡፡ የህወሃት ማእከላይ ኮሚቴ ከመጋቢት30-ሚያዝያ 3/2011ዓ.ም ተሰብስቦ ባወጣው መግለጫ ከፊል ይዘቱ እንዲህ ይላል፡-

“ስር-ነቀል ተሀድሶ ጀምረናል” ይልና ወረድ ብሎ “ህወሐትና የትግራይ ህዝብን ለማንበርከክ ከሁሉም ማእዘን ጥቃት ተሰንዝሮብናል፣ . . .የሚተባበርዋቸው ታሪካዊ ክህደት እየፈፀሙ ነው፤ . . . በፖለቲካ ሽፋን ለንግድና ሸቀጥ የተሰማሩ እንክርዳዶች ከደቡብና ሰሜን የተላኩ ባንዳዎች ተቀጥረው ይንቀሳቀሳሉ” ይላል፡፡ አለፍ ብሎ ደግሞ ኢህአዴግ ወደ ቦታው እንዲመለስ ማድረግ . . . ህገ-መንግስቱና ፌደራላዊ ስርአቱ ሳይሸራረፍ ተግባር ላይ በማዋል ሀገራዊ ዋስትና ማረጋገጥ ነው የሚቻለው” ይላል፡፡ በተለይ ሙሉውን መግለጫው ላነበበ ሰው የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ምንኛ በቅጡ ማሰብ እንደተሳነውና በድንጋጤ እንደተዋጠ ያመላክታል፡፡

1ኛ. ህወሓትና የትግራይ ህዝብ ለየቅል መሆኑን እስካሁን አልገባውም፤ ህወሓት እንደሆን በአንድ ወቅት የተፈጠረ በሌላ ወቅት የሚከስም የትግል መሳርያና ስልጣን ፈላጊ ድርጅት ሲሆን፤ የትግራይ ህዝብ ግን ጥንት የኖረ ወደፊትም የሚኖር የተለያዩ ድርጅቶች ማስተናገድ የሚችል ዘላቂ ሕብረተሰብ ነው፡፡ ለመመሸግያ ተብሎ ህወሓትና የትግራይ ህዝብ አንድ አድርጎ ማቅረብ የማያዛልቅ ቅጥፈት ነው፡፡

2ኛ. ሁሌ እያፈኑና እየዘረፉ፣ በስልጣን እየባለጉ፣ ሁሌ ተሃድሶ (አንዴ በጥልቀት፣ ሌላ ጊዜ ስር-ነቀል) ማለቱ ራስን ማሞኘት ካልሆነ በስተቀር ሌላ የሚታለል ስለሌለ በቅጥፈቱ ክልል ውስጥ ይካተታል፡፡ የ27አመታት አፋኝ አገዛዝ ከበቂ በላይ አስረጂ ነው፡፡

3ኛ. ከሁሉም ማእዘን ጥቃት ተሰንዝሮብናል የሚለው የማስደንገጫ ደወል ህዝቡን በፍርሃት ድባብ ውስጥ ለመከተት የተጠነጠነ መሰሪ ሴራ እንጂ በህዝባችን ላይ ያነጣጠረ ጥቃት አይታይም፤ ሰርቶና አርሶ አዳሪው ህዝባችን ማንንም አልበደለም፣ ማንኛውም ህዝብ በሱ ላይ አልተነሳም፡፡ በርግጥ የጥቂት ፅንፈኞች ቀረርቶ ድሮም ይሁን አሁን ይደመጣል። ፅንፈኝነት ደግሞ ከመሃከላችንም አይጠፋም - የመገንጠል አቀንቃኞችን ይመለከታል። ህዝባችን ተባብሮ ለሙብቱ መከበር ከቆመ ፅንፈኝነት ከየትም ቢመጣ ቦታ አያገኝም፡፡ ፅንፈኝነት ማፍረስ እንጂ መገንባት ስለማያውቅ መቸውንም ቢሆን አይቀናውም፡፡

4ኛ. ክህደት የፈፀሙ እንክርዳድ ባንዳዎች የሚባሉትስ እነማን ይሆኑ? መብቱ ለማስከበር ከድህነት ለመላቀቅ የታገለ ህዝብን ረስቶ፣ አሁንም መብቱን ረግጦ በድህነት እንዲቀጥል ያስገደደ አይደል እንዴ ከሃዲ የሚባለው? ወደ ታሪካዊ ዝርዝር ሳንገባ፣ የሃገሩን ባህር በር አሳልፎ የሰጠ፤ ሃገሩን ወደብ-አልባ ያደረገ የለየት ባንዳ ካልተባለ ባንዳነቱን ለማን ሊሰጥ ነው?

5ኛ. ኢህአዴግ ወደ ቦታው እንዲመለስ ማድረግ ምን ማለት ነው? ኢህአዴግ በቦታው አይደል እንዴ ያለው? ይህ መግለጫ በምንፅፍበት ወቅት ሳይቀር አዲስ አበባ ላይ ጉባኤ ተቀምጠዋል፡፡ ህገ-መንግስቱና ፌደራላዊ ስርአቱ መሰረት በማድረግ አራቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች /ህወሀትን ጨምሮ/ እየመከሩ ነው፡፡ ቀውስ ፈጣሪዎች ራሳቸው ቀውሰው ካልሆኑ በስተቀር ኢህአዴግ ወዴት ይመለሳል?

ህገ-መንገስቱ በተመለከት ሲያፈርስ የኖረውና አሁንም በማፍረስ ላይ የሚገኘው የህወሃት አመራር ራሱ እንደሆነ ሁሉም የሚያውቀው ሀቅ ነው፡፡ ማስረጃ ካስፈለገም ህገ-መንግስቱ የደነገገው አንቀፅ 27 መመልከት በቂ ነው፤ አንቀጹ. . . ማንም ሰው የሀይማኖት የእምነት የሃሰብ ነፃነት አለው ይላል፡፡ የትግራይ ህዝብ ሀሳቡን በነፃነት እንዳይገልፅ በማፈን፣ አማራጭ ድርጅት እንዳይኖሮውና ህዝቡ የመረጠውን ፓርቲ ለስልጣን እንዳያበቃ አፍኖ የያዘው ራሱ የህወሓት አመራር ነው፤ ህወሓትና የትግራይ ህዝብ አንድ ነው እያለ የሚያወናብደው በሙስና የበሰበሰ አመራር፣ ህዝቡና የበሰበሰው አመራር አንድ ሊሆኑ እንደማይችሉ የሚያጋልጡ የህዝብ ወገኖችን የሚደበድብ፣ የሚገድል፣ የሚያስር፣ ለአስከፊ ስደት የሚዳርግ ፀረ-ዲሞክራሲ ቡድን ራሱ የህወሓት አመራር ነው፡፡

ባለፈው እሁድ የኮሃ ህዝብ የጠ/ሚ አብይ አህመድ አካባቢን የማፅዳት ጥሪ ተቀብሎ በተሰማራው ህዝብ ላይ ህወሓት ያሰማራቸው ቅጥረኞች በህዝቡ ላይ ይህነው የማይባል ጥቃት አድርሰዋል፣ ብዙዎችንም አስረዋል፡፡ ቀደም ሲል የአመራሩ ብኩንነትና አቅመ ቢስነት በፖሊሲ ደረጃ ሲተቹ በነበሩ እንደነ ነቢዩ ስሑል፣ ፅጋቡ ቆባዕ /የዓረና አባል/ አካለዊ ጉዳት አድርሶውባቸው ወጣቶቹ ዓይደር ሆስፒታል ገብተው በመታከም ላይ ይገኛሉ፡፡ በዛው እለት ተደብድበው ጉዳት የደረሰባቸው፣ ሽዋዓለም ለማን ጨምሮ ሌሎች 21 ወጣቶች እቤታቸው ተኝተው በማገገም ላይ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ ኢፍትሀዊ ተግባር በተለይ የመሬት ነጠቃን አስመልክቶ ፍትህ በማጣት የተበሳጩት ፣

1ኛ. ወ/ሮ አማከለች ታደሰ ራሳቸውን ሰቅለው ሂወታቸውን ሲያጠፉ፤

2ኛ. ወ/ሮ ፀሊላ አብራሃለይ ደግሞ በብስጭት ብዛት የአካል መንቀጥቀጥ አጥቅቶዋቸው አቤቱታ ለማሰማት በሄዱበት የአስተዳደሩ መ/ቤት በራፍ ላይ ወድቀው ሂወታቸው አልፎዋል፡፡

የህወሓት አመራር ለ27ዓመታት በህዝባችን ጫንቃ ላይ ተኮፍሶ ያወረደውን ግፍ እንዳይበቃ አሁንም በዛው ላይ ሌላ ግፍ እያወረደ በስልጣን ላይ መቆየት እንደመረጠ በመግለጫው ግልፅ አድርጎዋል፡፡ በመላው ኢትዮጵያ የነፈሰው የለውጥ አየርም በትግራይ እንዳይነፍስ አግቶ በመያዝና የጦርነት ወሬ በመንዛት፣ ህዝብን በማስፈራራት፣ ለውጥ ፈላጊ ወጣት በመደብደብ- በማሰር- በመግደል- በማጉላላት፣ ወገኑ ከሆነው የአፋር፣ የአማራና የኤርትራ ህዝብ ጋር በማጋጨት እኩይ ስራውን ቀጥሎበታል፡፡ ይህ ጋህድ የወጣው እኩይ የህወሓት አመራር ተግባር በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደተጠላ የታወቀ በመሆኑ

አመራሩ ቀቢፅ ተስፋ ሆኖ የሚወስዳቸው እርምጃዎችም የዚህ ቀውስ ነፀብራቅ  እንደሚሆኑ ድሮውንም የሚታወቅ ነው፡፡

በትግራይ ህዝብ ባጠቃላይ፣ በተለይም በወጣቱ ትውልድ ላይ በህወሓት አመራር እየተወሰደ ያለው ጭካኔ የተሞላው የድብደባ፣ የእስር እና የግድያ እርምጃዎች የዴሞክራሲና የአንድነት ትግሉን ያጠነክረዋል እንጂ በምንም መንገድ ሊገታው አይችልም። ህወሓት አሁን በእስር ቤት ያጎራቸውን ወጣቶች በአስቸኳይ እንዲፈታ፣ በፖሊስ ድብደባ ለተጎዱትም ህክምና እንዲደረግላቸውና ተገቢ ካሳ እንዲከፍላቸው፣ እንዲሁም ይህንን አሰቃቂ ግፍ የፈጸሙትን በህግ እንዲጠየቁ ዓረና ትግራይ እና የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር እንጠይቃለን።

በማያያዝም፣ በትግራይ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ተደራራቢ ግፍ በመገንዘብ፣ ብሎም ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲመሰረት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማህበራትና ለፍትሃዊ ስርአት መመስረት የሚተጋ ሁሉ ወገኑ ለሆነው የትግራይ ህዝብ ለሚያደርገው ትግል አጋርነቱን በግልፅ እንዲያሳይ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

- ✓ የትግራይ ህዝብ ከአምባገነኑ የህወሓት አመራር ነፃ ይወጣል ፣
- ✓ ኢትዮጵያ በተባበሩት ልጆችዋ ክንድ ትበለፅጋለች፣

9 ሚያዝያ 2011